**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**FEDERAL SUPREME COURT**

የሰበር መዝገብ ቁጥር 239542

ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሡፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ሙሉሰው አንዷለም ጠበቃ አቶ ገበያው ይታየው

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰናይት አምሳሉ ጠበቃ ሰለሞን መሰረት ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ፍቺና የፍቺ ውጤትን የሚመለከት የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን ክሱ በቀረበበት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ ፣ አመለካች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀር መሆኑን ተከትሎ ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 ጣና ገበያ ተብሎ ከሚጣራው የገበያ ማዕከል በእሳቸው እና በእህታቸው ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ ስም የተመዘገበው የሱቅ ቁጥር 52 የግል ንብረታቸው መሆኑን ገልፀው አመልካች

እንዲያስረክባቸው ፤ እንዲሁም ሌሎች የጋራ ናቸው የሚሉትን ንብረቶች በመዘርዘር ግማሽ የሚስትነት ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ያቀረቡት የንብረት ዝርዝር በተመለከተ በሰጡት ምላሽ በደብረ ማርቆስ ከተማ ጣና ገበያ የሱቅ ቁጥር 52 ከተጠሪ እህት ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ ጋር ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገ ክፍፍል ለግራ ቀኙ የደረሰን የጋራ ሀብት በመሆኑ በዓይነት መካፈል ከተቻለ በዓይነት እንዲካፈሉ እንዲወሰንላቸው ፤ ሌሎች ለሰበር ክርክሩ ምክንያት ያልሆኑ ንብረቶችን በተመለከ ዝርዝር መልስ የሰጡ ሲሆን ተጠሪ ባቀረቡት ዝርዝር ያልተካተቱ የጋራ የሏቸውን ንብረቶችንም በመዘርዘር ድርሻቸው እንዲወስንላቸው የጠየቁ ሲሆን ፤ ተጠሪም በአመልካች በኩል በቀረበው የንብረት ዝርዝር ላይ ያላቸውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ እንዲሁም የማጣሪያ ምስክሮች ስምቶ እና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ካደረገ በኋላ መዝገቡን እንደመረመረው፡- ግራ ቀኙ የተሰፉ ልብሶች እና የቤት ዕቃዎችን በሽማግሌ የተከፋፈሉ መሆኑ በሰው እና የሰነድ ማስረጃ ስለተረጋገጠ እንዲሁም በክፍፍሉ ወቅትም የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ በድጋሚ  የክፍፍል ጥያቄ ልቀርብ አይገባም ፤ ክፍፍል ያልተደረገባቸው የጋራ ሀብት መኖራቸው የተረጋገጡ ንብረቶችን እኩል እንዲካፈሉ ፤ በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውን የሱቅ ቁጥር 52 በሻጭ እና ገዥ መካከል ግልጽ የሖነ የሽያጭ ውል አለመኖሩን ፣ ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም ተደረጓል የተባለው የሽያጭ ውል ተጠሪ እና ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ ሱቅ የተከፋፈሉ መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ፣ በሱቅ ክፍፍሉ ላይ የነበሩ ሽማግሌዎች የሱቅ ክፍፍል መደረጉን እንጅ ሱቁ በምን አግባብ እንደተገኘ እንዳማያውቁ ፣ ፎቅ ላይ ያለውን ለወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ የመሬቱን ለተጠሪ ማከፋፈላቸውን ፣ በሻጭ እና ገዥ መካከል የሽያጭ ውል አለመኖሩን ፣ ተጠሪ እና እህታቸው ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ በተደጋጋሚ በዚህ ሱቅ እንዲነግዱበት አባታቸውን ጠይቀው የተፈቀደላቸው መሆኑን ፣ ይህ የሖነው አከራይ ተከራይ እንዳይከፍሉ ፣ በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው እንዲነግዱ ፣ ሱቁ ተመዝግቦ የሚገኘው በብርሃን አምሳሉ በመሆኑ ውክልና ለመስጠት በመቸገራቸው በቤተሰብ ተስማምተው ያለምንም ክፍያ ወይንም ሽያጭ በስማቸው የዞረ እንጅ አመልካች እና ተጠሪ ለሻጭ ምንም ዓይነት ገንዘብ ያልከፈሉ ሲሆን ፤ ከደብረ ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የቀረበው የሰነድ ማስረጃም በተጠሪ ወ/ሮ ሰናይት አምሳሉ እና በእህታቸው ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ ስም መዞሩን እንጅ ሽያጭ

መደረጉን ስለማያመለክት እና ጉዳዩም በቤተሰብ ስምምነት የተደረገ የስም ማዞር ተግባር እንጅ ሽያጭ ካለመሆኑም በላይ አመልካች G+1 የሖነውን ሱቅ ተገዝቶበታል የሚሉበት ብር 161,000.00(አንድ መቶ ስልሳ አንድ ሺ) ተመጣጣኝ ገንዘብ ባለመሆኑና አመልካች የተማሩ ከመሆናቸው አንፃር የገንዘብ ክፍያውን እማኝ በሌለበት ያለ ፊርማ አድርገዋል መባሉ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ሱቁን ለአመልካች ሊያካፍሉ አይገባም በማለት አልፎ ፤ የተጠሪ የግል ንብረት ለሆነው ቤት እድሳት በጋብቻ ውስጥ የወጣውን 39,030.00(ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ሰላሳ) ብር ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ለልጅ ቀለብ 1,200.00(አንድ ሺ ሁለት መቶ) ብር እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል 700.00(ሰባት መቶ) ብር የልጅ ቀለብ እንዲከፍሉ የወሰነ ሲሆን ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት የተጠሪ የግል ንብረት የሆነውን ቤት ለማጠናቀቅ በጋብቻ ውስጥ በተጠሪ አባት የወጣው 65,000.00(ስልሳ አምስት ሺ) ብር ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር ቅሬታው የቀረበውም ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሆኖ የቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው በጣና የገበያ ማዕከል ውስጥ የሚገኘው የሱቅ ቁጥር 52 የተጠሪ እህት የሖኑት ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ ከገበያ ማዕከሉ የነበራቸውን ቁጥራቸው 52 እና 152 የሖኑ ሁለት ሱቆችን የተጠሪ ሌላኛዋ እህት ከሆኑት ወ/ሮ ሐይማኖች አምሳሉ ጋር በጋራ ገዝተው ምድር ቤቱ ለአመልካች እና ለተጠሪ ፣ ፎቁ ደግሞ ለወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ እንዲሆን ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም ስምምት አድርገናል፡፡ ይህ በግራ ቀኙ ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም የተደረገው ስምምት አርእስቱ የግዥ ውል የሚል ሆኖ ገዥዎች ተጠሪ እና ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን ፤ ውሉም ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ለደብረ ማርቆስ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቀርቦ በውል ሰጪዎች ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ እና ባለቤታቸው እንዲሁም በውል ተቀባዮች ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ እና ተጠሪ ተፈርሞ ተገቢው የመንግስት ክፍያ ተፈጽሞ ስመንብረቱ ወደ ተጠሪ ዞሯል፡፡ ይህ የሖነው አመልካች እና ተጠሪ ከተገባን ከሶስት ዓመት በኋላ ሆኖ ተጠሪ ቤቱን በግዷ ያገኘች ለመሆኑ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ሻጯም የሽያጭ ውሉን አልተቃወሙም፡፡ የተጠሪ ወላጅ አባትም በአከራካሪው ሱቅ ላይ መብት እና ጥቅም አለኝ በማለት ወደ ክርክሩ

ገብተው ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ አመልካች ሱቁን ልካፈሉ አይገባም ከማለት አልፎ ሱቁ ለተጠሪ አባትም አልተወሰነም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ሱቁን ልካፈል አይገባም በማለት የወሰነው የተጠሪ ወላጅ አባት የሖኑት አምሳሉ ሁነኛው ለልጆቻቸው በስጦታ አስተላልፈዉላቸዋል በሚል ቢሆንም ሱቁ የአቶ አምሳሉ ሁነኛው የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ አንድም ተጨባጭ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ አቶ አምሳሉ ሁነኛው ለወ/ሮ ብርሃንም ሆነ በኋላ ቤቱን ለገዙት ተጠሪ እና ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ በስጦታ ያስተላለፉ ለመሆናቸው አንዳችም የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ አቶ አምሳሉ ሁነኛው ለተጠሪ እና ሌላኛዋ እህታቸው ሱቁን ሲገዙ ገንዘብ ከፍየላቸዋለሁኝ በማለት የቀረበው ክርክርም የማስረጃ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል አቶ አምሳሉ ሁነኛው ይህ ቤት እና ቦታ ሲገዛ ገንዘብ አዋጭቻለሁ ካሉ ገንዘቡን የከፈሉለት ግለሰብ እንዲመልስላቸው መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀበት በመሆኑ ውሳኔ ተሽሮ ለክርክሩ ምክንያት የሖነው ሱቅ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ሱቁ የጋራ ሀብት አይደለም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት ተጠሪ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ታዘው ተከታዩን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፡- አከራካሪው ሱቅ በግዥ የተገኘ ለመሆኑ በአመልካች በኩል  የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ የሱቁ ሻጭ ናቸው የተባለት ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ ሱቁን በሽያጭ እንዳላስተላለፉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሱቁ በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቢሆንም የወላጅ አባቴ ሆኖ እራሳቸውን ያልቻሉ ልጆች እራሳቸውን እስክችሉ ድረስ እንዲጠቀሙበት ታስቦ ተጠሪ አመልችን ሳገባ ምንም ዓይነት ገቢ ስላልነበረኝ በአከራካሪው ሱቅ ሰርታ እራሷን ከቻለችው እህቴ ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ ተላልፎልኝ እየተጠቀምኩበት ያለሁ እንጅ በግል ገንዘባች የተገዛ አይደለም፡፡ ሱቁ የተገዛበት የሽያጭ ውል ካለመቅረቡም በላይ ሱቁ ወደ ተጠሪ ስም የዞረው የሽያጭ ውልን መሠረት አድርጎ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃም አልቀረበም፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ቀርቧል የሚሉት የክፍፍል ስምምነት እንጅ የሽያጭ ባለመሆኑ  አካራካሪው ሱቅ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ባለመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ሆኖ ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሖነው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቀርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(2) ድንጋጌ መሠረት የግል ንብረት ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይንም ንብረት የማፍራት መብት የተሰጣቸው ማህበራት በጉልበታቸው ፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይንም በካፒታላቸው ያፈሩት ንብረት መሆኑ ተደግጓል። በዚህ መልክ የተገኘ ባለሃብትነት በህግ ከተመለከቱት ሥርዓቶች ውጭ ልገደብ የማይችል የሕግ ጥበቃ የተደረገለት ሰፊ መብት እንደሆነ የፍትሐብሔ ሕግ ቁጥር 1204 ያስገነዝበናል። ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች የሚተላለፍ ሲሆን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሀብትነት ሲተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 ያስገነዝበናል። በዚህ መልክ ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1553- 1636 ድንጋጌዎች መሠረት ነው። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የባለሀብትነት መብቱ እና ሌሎች በነዚህ ንብረቶች ላይ መብትን የሚያቃቁሙ ሕጋዊያን ተግባሮች በጽሁፍ ሆኖ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ሰፍሮ የነዚህ መብቶች መኖር በተለየ ማስረጃ እንድረጋገጥ መደረጉ ሕጉ ለነዚህ ንብረቶች የተለየ ጥበቃ እደሚያደርግ ማሳያ ነው። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ እንደምቆጠር ከፍ/ሕ/ሕግ ቁጥር 1195 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1195 የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል ስሆን በፍ/ሕ/ ሕግ ቁጥር 1196 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸዉን በማንኛውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል ይችላል።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 53(1) መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻዉ ንብረትን በተመለከተ ያሚያስከትለዉን ዉጤት ከጋብቻቸዉ በፊት ወይንም

በጋብታቸዉ ዕለት በዉል መወሰን ይችላሉ። ጋብቻ በሚፈፀሙበት ጊዜ በግል የነበራቸዉ እና በጋብቻ ዉስጥ በግል በዉርስ ወይንም ስጦታ ያገኙት ንብረት የግል መሆኑን አንቀጽ 68 ይስረዳናል። በባል እና ሚስቱ ከግል ጥረታቸውና ግል ወይንም ከጋራ ንብረታቸው የሚገኙ ገቢዎች ፤ እንዲሁም የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በቀር ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚገኙ ንብረቶች በሙሉ የጋራ ሀብት እንደሆኑ አንቀጽ 73 (1) እና (2) ይደነግጋል። አንደኛው ተጋቢ የግሉ መሆኑን ካላስረዳ በቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ እንደሚቆጠር ከአንቀጽ 74(1) ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ የጋብቻ መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክቶ ባልና ሚስት በሚያደርጉት ስምምነት ወይንም በጋብቻ ውላቸው መሠረት የባልና ሚስት ሀብት እንደሚጣራ አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ባል እና ሚስት ጋብቻቸዉ በሕግ ፀንቶ ባለ ጊዜ በንብረታቸዉ ላይ የጋራ ባለሀብት ከመሆን ባለፈ እንደ የጋራ ባለሀብቶች የንብረት ድርሻቸዉ መጠን ያልተከፋፈለ እና ተለይቶ የሚታወቅ ባለመሆኑ በኢ/ፌ/ዴ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35(2) እና አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 101 ባል እና ሚስት በጋራ ሀብታቸዉ ላይ እኩል መብት ስላላቸዉ በፍቺ ጊዜ እኩል ይካፈላሉ። የክፍፍል ሥርዓቱም በአንቀጽ 102 እና 103 ድንጋጌ መሠረት ከተቻለ በአይነት ፣ የዓይነት ክፍፍሉ የማይቻል ከሆነ በስምምነት የንብረቱ ግምት በመዉሰድ ንብረቱ ለሌላዉ በመተዉ ፣ መስማማት ካልተቻለ በሐራጅ ተሽጦ ገንዘቡ የሚከፋፈል ሆኖ የእኩልነት መሪህን መሠረት አድርጎ ነዉ። የጋራ ንብረት እኩል እንዲከፋፈል የሚደረግበት ዋናዉ ምክንያት ባል እና ሚስቱ በንብረት መፈራት ሂደት እኩል አስተዋጾ ነበራቸዉ ከሚል እምነት የመነጨ ነዉ። ክፍፍሉ ፍትሓዊ ፣ አንዱ በሌላዉ ድካም አላግባብ እንዳይበለጽግ የማያደርግ እንዱሁም መሠረታዊ እና ሰፌ የሆነዉን የንብረት እና ባለሀብነት መብትን የማይገድብ መሆን አለበት።

በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 ጣና ገበያ ተብሎ ከሚጣራው የገበያ ማዕከል በእሳቸው እና እህታቸው ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ ስም የተመዘገበው የሱቅ ቁጥር 52 የግል ንብረታቸው መሆኑን ገልፀው አመልካች እንዲያስረክባቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ያቀረቡት የንብረት ዝርዝር በተመለከተ በሰጡት ምላሽ በደብረ ማርቆስ ከተማ

ጣና ገበያ የሱቅ ቁጥር 52 ከተጠሪ እህት ወ/ሮ ብርሃን አምሳሉ ጋር ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገ ክፍፍል ለግራ ቀኙ የደረሰን የጋራ ሀብት በመሆኑ በዓይነት መካፈል ከተቻለ በዓይነት እንዲካፈሉ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ የደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውን የሱቅ ቁጥር 52 አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በሚል ውሳኔ የሰጠው ሱቁ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑ ስለተረጋገጠ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አይደለም በሚል ሳይሆን ፤ በሻጭ እና ገዥ መካከል ግልጽ የሆነ የሽያጭ ውል አለመኖሩን ፣ ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም የተደረገው ውል የሽያጭ ሳይሆን በተጠሪ እና ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ መካከል የተደረገ የሱቅ ክፍፍል መሆኑን ፣ ክፍፍል የተደረገበት ሱቅ የተገኘበት አግባብ አለመታወቁን ፣ ሱቁ ለተጠሪ እና እህታቸው ወ/ሮ ሐይማኖት አምሳሉ በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው እንዲነግዱበት በአባታቸው ተፈቅዶላቸው ቤተሰብ ተስማምተው ያለምንም ክፍያ ወይንም ሽያጭ በስማቸው የዞረ እንጅ አመልካች እና ተጠሪ ለሻጭ ምንም ዓይነት ገንዘብ አለመከፈሉን ፣ ለግዥው ውሏል የተባለው ብር 161,000.00(አንድ መቶ ስልሳ አንድ ሺ) G+1 ሱቅ ጋር ተመጣጣኝ አለመሆኑን ፣ አመልካች የተማሩ ከመሆናቸው አንፃር የገንዘብ ክፍያውን እማኝ በሌለበት ያለ ፊርማ ያደርጋሉ ተብሎ አይታመንም በሚል ነው፡፡

የእነዚህ ከላይ የተመለከቱ ፍሬ ነገሮች ተሟልቶ አለመገኘት ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ሱቅ የተጠሪ የግል ንብረት ያደርገዋል ወደሚል ድምዳሜ የማያደርስ ሲሆን ፤ የሥር ፍርድ ቤቶች ሱቁ የተጠሪ የግል ንብረት ነው የሚል ውሳኔ አልሰጡም፡፡ በአንደኛው ተጋቢ ስም ንብረት ተመዝግቦ መገኘቱ ብቻ ንብረቱን የግል ስለማያደርገው የግሌ ነው የሚለው ተጋቢ የግሉ መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ተጠሪ አከራካሪው ሱቅ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የግላቸው መሆኑን እንደክርክራቸው አላስረዱም፡፡ በሌለ በኩል ከአመልካች እና ተጠሪ ውጭ ሱቁ ይገባኛል የሚል ወይንም ሱቁ ወደ ተጠሪ የተላለፈበት ሂደት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ቀርቦ የተከራከረ ሰው ሳይኖር ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ወደ ተጠሪ ስም ዞሮ በስማቸው ተመዝግቦ ያለው ሱቅ ከላይ የተጠቀሱ ምክንያቶችን ጠቅሶ አመልካች የባልነት ድርሻቸውን እንዳያገኙ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነውን የአመልክችን የንብረት መብት የሚገድብ በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 112695 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘው የሱቅ ቁጥር 52 ውጪ ያላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘው የሱቅ ቁጥር 52 የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ በሕጉ በተመለከተው አግባብ ግራ ቀኙ እንዲከፋፈሉ ተወስኗል፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ላስከተለዉ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ